# የባለቅኔው ዝምታ



መጣልሽ እምዬ፣ ገሞራው ልጅሽ

ቅኔ ባኩፋዳ፣ ስንቁን ይዞልሽ፤

መጣልሽ ከርታቴ፣ አገር ላገር ማስኖ

በሰንዱቅ ሳጥኑ፣ ጨምቶ ተከድኖ፤

ያን ግርማ ያን ሞገስ፣ ያን መረዋ ድምጹን

ላንቺ አፈር ተናዞ፣ መጣልሽ ማታውን፤

”ሥጋዬ ካፈርሽ፣ ጥንት እንደተሠራ

መጣሁ ተቀበዪኝ፣ ካንቺጋ ልጠራ”

እያለ ማጾነ፣ አፍቃሪ እናቱን

በቃኝ አለ ዘጋ፣ የስደት ቤቱን፤

አርባ አመታት ሙሉ፣ ሲባዝን ሲቆዝም

መቼም አልተመቸው፣ ልጅ የለው ጉልቻ

ብሶት ብስጭቱ፣ አርጎት የራስ ብቻ፤

ያርባ ዓመታት ናፍቆት፣ የሕዝቡ ያገሩ

የወንዝ የተራራው ፣ የመስኩ ያየሩ

እኮ እንዴት ተቻለው፣ ምንድነው ምስጢሩ?

* * *

ላልተመቸህ ሥርዓት፣ የላላ ስትወጥር

የተወጠረውን በቅኔህ ስትመትር

የእርግማን በረከት፣ ስትለግስ ስትቸር

አኮ አገኘኸው ወይ የሕይወትን ምስጢር

ሁሌ ከራስህ ጋር፣ ስትጨምት ስትመክር?

መጣልሽ እምዬ፣ ገሞራው ልጅሽ

ቅኔ ባኩፋዳ፣ ስንቁን ይዞልሽ፤

መጣልሽ ከርታቴ፣ አገር ላገር ማስኖ

በሳንዱቅ ሳጥኑ፣ ጨምቶ ተከድኖ፤

ቻልከው ቻልከውና፣ አልከው አልከውና

ቅኔው ሞልቶ ቢፈስ፣ አንተው ፈሰስክና

መሸ ልረፍ አልከን፣ የማታ የማታ

የሰባመት ጉዞህ፣ የእድሜ ልክ ፍልሚያህ-

ባያ ሞት ሲገታ፤

ምኑ ነው እሚቆጭህ፣ ምኑ ነው እሚቀርህ

ሚሊዮን አንቅተህ፣ ያይን ሞራ ገልጠህ

ያሻህን ተቀኝተህ፣ ከዘመን ተሟግተህ

ተፈርተህ ተከብረህ፣ ተወደህ አልፈሃል

ገድልህን ፈጽመህ፣ ዛሬ አሸልበሃል

እንቅልፍ ለምኔው፣ እጅህን ሰጥተሃል

ዛሬ በታሪክ ወስጥ፣ አንድ ቀን ወድቀሃል

ሸንፈት እማታውቀው፣ ምርኮኛ ሆነሃል

እነሆ ተንጋለህ፣ እፎይታን መርጠሃል፤

መጣልሽ እምዬ፣ ገሞራው ልጅሽ
ቅኔ ባኩፋዳ፣ ስንቁን ይዞልሽ፤
መጣልሽ ከርታቴ፣ አገር ላገር ማስኖ
በሳንዱቅ ሳጥኑ፣ ጨምቶ ተከድኖ፤

ሂድ እንጂ ጋሽዬ፣ እንደኮራህ ግባ
ሸገር ናፍቃሃለች፣ ያባቶችህ ቀዬ-
ያባቶችህ አምባ!
ሂድ እንጂ ጋሽዬ፣ ማን ከልካይ አለብህ
እንደወጡ መቅረት፣ ከቶም አያምርብህ!
ሂድ እንጂ ጋሽዬ፣  የእውቀት ማህደሩ
ግባ ከእናት ጓዳ፣ ይመቻል አፈሩ!
ሂድ እንጂ ጋሽዬ፣ ሕዝብ ይጠብቅሃል
ያገርህ አሞራ፣ ዋይታዋ ጠንክሯል!
ቱቢት አስመትታ፣ ሙሾ እያወረደች
ኃይልዬን ጥበቃ፣ እሷም ታድማለች፤

መጣልሽ እምዬ፣ ገሞራው ልጅሽ
ቅኔ ባኩፋዳ፣ ስንቁን ይዞልሽ፤
መጣልሽ ከርታቴ፣ አገር ላገር ማስኖ
በሳንዱቅ ሳጥኑ፣ ጨምቶ ተከድኖ፤

በሉዋ ወዳጆቹ፣ በሉዋ ጓደኖቹ
የቆማችሁ፣ ከዘመድ አዝማዶቹ
"ሞትም ይሙት!..." እያለችሁ
በዶርዝኛ ስልት ቃኝታችሁ
በፀጋዬኛ ዘምሩለት፣ እባካችሁ
ደስ ብሎት፣ ጋሽ ኃይልዬ ይለያችሁ፤
የባለቅኔው ኩርፊያ፣ የባለቅኔው ዝምታ
በሞትም ይሙት ረገዳ፣ ሃዘን ሰቀቃው ይረታ፤

መጣልሽ እምዬ፣ ገሞራው ልጅሽ
ቅኔ ባኩፋዳ፣ ስንቁን ይዞልሽ፤
መጣልሽ ከርታቴ፣ አገር ላገር ማስኖ
በሳንዱቅ ሳጥኑ፣ ጨምቶ ተከድኖ፤

-በአበራ ለማ

ለጋሼ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ መሸኛ መታሰቢያ

(እስቶክሆልም፣ ስዊድን፣ ሕዳር 20 ቀን 2007 ዓ.ም.)